- አይሄድም።

- ለምን አይሄድም?

- ምክንያቱም ሕመምተኛ መሆኑን ስለማያውቅ ነው።

- ኢየሱስ ኃጢአት እንደሌለባቸው የሚያምኑትን ሰዎች ለማዳን አልመጣም።

- ኢየሱስ የመጣው ማንን ሊያድን ነው?

- ኢየሱስ የመጣው፥ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራታቸውንና እግዚአብሔር ብቻ ሊያድናቸው እንደሚችል ያመኑትን ሰዎች ሊያድን ነው።

- እናንተስ?

- ኃጢአተኛ ሆናችሁ መወለዳችሁን ታውቃላችሁ?

- እግዚአብሔርን እንደ በደላችሁ ታውቃላችሁ?

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በዘላለም ሞት እንደሚቀጣ ታውቃላችሁ?

- አዳኙ እግዚአብሔር ብቻ ሊያድናችሁ እንደሚችል ታውቃላችሁ?

- ኢየሱስ “የእናንተ አዳኝ በመሆን ወደዚህ ዓለም መጥቻለሁ” ይላችኋል።



## ትምህርት 52

1. ኒቆዲሞስ ኢየሱስን እግዚአብሔር እንደ ላከው በምን አወቀ?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራ የሚችለውን ተአምራት ይሠራ ስለ ነበር።

2. «ከውኃ መወለድ» ማለት «መጠመቅ» ማለት ነው?

ሀ- አይደለም።

3. ጥምቀት ሊያድነን ይችላል?

ሀ- አይችልም።

4. ኢየሱስ «ከውኃ መወለድ» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ- ከውኃ መወለድ ማለት እግዚአብሔር ከኃጢአታችን እንዲያነጻን ንስሐ መግባት ማለት ነው።

5. ኢየሱስ «ከመንፈስ መወለድ» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ- ከመንፈስ መወለድ ማለት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችን አዲስ ሕይወት መስጠት ማለት ነው።

6. ኢየሱስ «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ- ሥጋ መውለድ የሚችለው ሥጋን ብቻ ነው ማለቱ ነው፥

ለ -ደግሞም ኢየሱስ፥ ለሰው መንፈስ አዲስ ልደትን መስጠት የሚችለው የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው ማለቱ ነው።

7. እግዚአብሔር በዓለም ላይ አሉ ያላቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን ናቸው?

ሀ- አንድ ጊዜ ብቻ የተወለዱና ዳግም የተወለዱ ናቸው።

8. አንድ ጊዜ ብቻ የተወለዱት የማን ቤተሰብ አባላት ናቸው?

ሀ- የሰይጣን ቤተሰብ አባላት።

9. ዳግመኛ የተወለዱት የማን ቤተሰብ አባላት ናቸው?

ሀ- የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት።

10. ኢየሱስና ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀለው የናሱ እባብ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ሀ- የናሱ እባብ በእንጨት ላይ እንደ ተሰቀለ፣ ኢየሱስም ይሰቀላል።

ለ- እስራኤላውያን የናሱን እባብ ሲመለከቱ እንደ ዳኑ ሁሉ፣ ኢየሱስም በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ያድናቸዋል።

11. እግዚአብሔር ኢየሱስን ወደዚህ ዓለም የላከው ለምንድን ነው?

ሀ- ሰዎችን ከኃጢአት፣ ከሞትና ከሰይጣን ኃይል እንዲያድን ነው።

12. በኢየሱስ ባመኑት ላይ እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል?

ሀ- አይፈርድባቸውም።

13. በኢየሱስ ያላመኑት አሁኑኑ የተፈረደባቸው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ አዳኙ እግዚአብሔር መሆኑን ስላላመኑ ነው።

14. ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መስማት የማይፈልጉት ለምንድን ነው?

ሀ- ኃጢአታቸውን ስለሚወዱ ነው።

- አንድ ቀን ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም መንደር ተመለሰ።



- ፈሪሳውያን ኃጢአት እንደሌለባቸው ያምኑ ነበር።

- ፈሪሳውያን ሰዎች ሁሉ በኃጢአት መወለዳቸውን አልተረዱም።

- ፈሪሳውያን ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራታቸውን አልተረዱም ነበር።

- ኢየሱስ ፈሪሳውያን የሚናገሩትን ሰምቶ ምን አለ?

ማርቆስ 2፡17

17- ኢየሱስም የሚናገሩትን ሰምቶ፣ «ሐኪም የሚያስፈልጋቸው ሕመምተኞች እንጂ ጤነኞች አይደሉም፤ እኔ ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ወደ ንስሓ ልጠራ አልመጣሁም» አላቸው።

- ኢየሱስ ለፈርሳውያን "ሕመምተኞች እንጂ ጤናማዎች ሐኪም አያስፈልጋቸውም" አላቸው።

- ኢየሱስ ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ "ሕመምተኛ መሆናቸውን ያላወቁትን ሰዎች ላድን አልመጣሁም" ማለቱ ነበር።

- ኢየሱስ ሊያድን የመጣው በሽተኛ መሆናቸውን ያወቁ ሰዎችን ብቻ ነው።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- አንድ ሰው ቢታመምም፥ መታመሙን ካላወቀ ለሕክምና ወደ ሐኪም ይሄዳል?

ስለተረዳ ነው።

- ምክንያቱም ማቴዎስ እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል ስለተረዳ ነው።

- ምክንያቱም ማቴዎስ ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ስለተረዳ ነው።

- ከብዙ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት አንዱን መጽሐፍ እንዲጽፍ ማቴዎስን መራው።

- ማቴዎስ ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ በመቀበሉ ስለ ተደሰ፣ ኢየሱስንና ሌሎችን ሰዎች በቤቱ ጋበዛቸው።

ማርቆስ 2፡15-16

15- ኢየሱስ በማቴዎስ ቤት በማእድ ተቀምጦ ሳለ፣ ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች ተከትለውት ስለ ነበር፣ ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ይመገቡ ነበር።

16- ከፈሪሳውያን ወገን የነበሩት ጸሐፍት ከኃጢአተኞችና ከቀረጥ ሰብሳቢዎች ጋር ሲበላ ባዩት ጊዜ፣ ደቀ መዛሙርቱን «ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኃጢአተኞች ጋር ለምን ይበላል?» ሲሉ ጠየቋቸው።

- የሕግ መምህራን የሆኑት ፈሪሳውያን ኢየሱስ ከማቴዎስና ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲመገብ ሲያዩ ምን አሉ?

- «ኢየሱስ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር የሚበላው ለምንድን ነው» አሉ?

- ፈሪሳውያን ኃጢአተኞች መሆናቸውን አላመኑም ነበር።



ማርቆስ 2፡1-2

1- ኢየሱስ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍርናሆም እንደ ተመለሰ፣ ወደ ቤት መግባቱን ሕዝቡ ሰማ።

2- ስለዚህ ከበሩ ውጭ እንኳ ሳይቀር ስፍራ እስኪታጣ ድረስ ብዙ ሕዝብ ተሰበሰበ፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ሰበከላቸው።

- ብዙ ሰዎች የኢየሱስን ትምህርት ለመስማት መጡ።

- ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል አስተማራቸው።

- ኢየሱስ ያስተማራቸው የእግዚአብሔር ቃል ዛሬ ለእናንተ እያስተማርናችሁ ያለነው ቃል ነው።

- የእግዚአብሔር ቃል አይለወጥም።

- የእግዚአብሔር ቃል ለሰዎች ሁሉ አንድ ዓይነት ነው።

- ሰዎች ኢየሱስ ሲያስተምር እንዳደመጡት ሁሉ፣ እናንተም የእግዚአብሔርን ቃል ስናስተምራችሁ እንድታደምጡ እግዚአብሔር ይፈልጋል።

- ኢየሱስ ያስተማራቸው በቤት ውስጥ ስለ ነበርና ብዙ ሰዎች የኢየሱስን ትምህርት ሊሰሙ ስለ መጡ፣ ቤት ውስጥ ምንም ስፍራ አልነበረም።

- ከበር ውጭ እንኳ ስፍራ አልነበረም።

- ኢየሱስ በማስተማር ላይ ሳለ፣ ጥቂት ሰዎች አንድ ሽባ ሰው አመጡ።

ማርቆስ 2፡3

3- ጥቂት ሰዎችም አንድ ሽባ በአራት ሰዎች አሸክመው ወደ እርሱ አመጡ።

- ሽባው ሰውዬ ራሱን መፈወስ ችሎአል?
- አልቻለም።

- የሽባው ሰው ወዳጆች እርሱን ሊፈውሱት ችለዋል?
- አልቻሉም።

- ሽባውን ሰው ማዳን የቻለ ሐኪም ነበር?
- አልነበረም።

- ይህ ሽባ ሰው ራሱን መፈወስ እንዳልቻለ ሁሉ ማንም ራሱን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ለማዳን አይችልም።

- ሰዎቹ ሽባውን ሰው ምን አደረጉት?

ማርቆስ 2፡4

4- ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ኢየሱስ ወዳለበት መቅረብ ስላልቻሉ፣ የቤቱን ጣራ እርሱ ባለበት በኩል ነድለው ቀዳዳ በማበጀት ሽባው የተኛበትን አልጋ በዚያ አወረዱ።

- እጅግ ብዙ ሰዎች ኢየሱስ ሲያስተምር ያደምጡ ስለ ነበርና ቤቱ ተጣብቦ ስለ ነበር፣ ሰዎቹ ሽባውን ሰው በቤቱ ጣሪያ ላይ አወጡት።



- ኢየሱስ በመንገድ ላይ ሲሄድ ሳለ ሌዊ የተባለውን ሰው አገኘ።

- የሌዊ ሁለተኛ ስሙ ማን ነበር?
- ማቴዎስ።

- ኢየሱስ በጠራው ጊዜ የማቴዎስ ሥራ ምን ነበር?
- ማቴዎስ ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር።

- ማቴዎስ ከራሱ ሕዝብ ከአይሁዶች ቀረጥ እየሰበሰበ ለሮማውያን ይሰጥ ነበር።

- ቀራጮች ከራሳቸው ሕዝብ ላይ ቀረጥ ሰብስበው ለሮማውያን ይሰጡ ስለ ነበር፣ አይሁዶች ይጠሏቸው ነበር።

- ቀራጮች በጣም ክፉዎች ስለ ነበሩ አይሁዶች ይጠሏቸው ነበር።

- ቀራጮች አይሁዶች ብዙ ቀረጥ እንዲከፍሉ አስገድደው ለራሳቸው ያስቀሩ ነበር።

- ኢየሱስ ቀራጩ ማቴዎስ እንዲከተለው ጠራው።

- ኢየሱስ ማቴዎስ እንዲከተለው የጠራው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ማቴዎስ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ስለተረዳ ነው።

- ምክንያቱም ማቴዎስ እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ

11- «ተነሥተህ ዐልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ» አለው።

12- እርሱም ተነሥቶ ሁሉም እያዩት አልጋውን ተሸክሞ ሄደ። በስፍራው የነበሩት ሁሉ በሁኔታው በመደነቅ “የዚህን አይነት ነገር ፈጽሞ አይተን አንውቅም” በማለት ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ።

- ኢየሱስ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር የማለት ሥልጣን እንዳለው ለሕዝቡ ተናገረ።

- ኢየሱስ ኃጢአት ይቅር የማለት ሥልጣን ሊኖረው የቻለው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ኢየሱስ ሽባውን ሰው ሙሉ በሙሉ ፈውሶ ኃይሉን አሳየ።

- ኢየሱስ በሽተኞችን መፈወስ የቻለው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ሽባውን መፈወስ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ከዚህ በኋላ፣ ኢየሱስ በቅፍርናሆም መንደር አጠገብ ወደሚገኝ ሐይቅ ሄደ።

ማርቆስ 2፡13-14

13- ኢየሱስም ዳግም ወደ ባሕሩ ዳርቻ ወጣ፤ ሕዝቡም በብዛት ወደ እርሱ መጡ፤ እርሱም አስተማራቸው።

14- በዚያም ሲያልፍ የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን በቀረጥ መቀበያው ስፍራ ተቀምጦ አየውና፣ «ተከተለኝ» አለው፤ እርሱም ተነሥቶ ተከተለው።



- ሰዎቹ የቤቱን ጣራ ነድለው (በስተው) ቀዳዳ በማበጀት፣ ሽባውን ሰው በተኛበት አልጋ በኢየሱስ ፊት አወረዱት።

- አይሁዶች የቤታቸውን ጣሪያ ከጭቃና ከገለባ ዝርግ አድርገው ይሠሩ ስለ ነበር፣ ሰዎቹ ጣሪያውን ለመብሳትና ሽባውን ኢየሱስ ፊት ለማውረድ ቻሉ።

- ሰዎቹ ሽባውን ሰው ያመጡት ወደ ማን ነበር?

- ወደ ኢየሱስ።

- ሽባውን ሰው ማዳን የቻለው ማን ብቻ ነበር?

- ኢየሱስ።

- ኢየሱስ ምን አደረገ?

ማርቆስ 2፡5

5- ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን፣ «አንተ ልጅ፣ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል» አለው።

- ኢየሱስ ሰዎቹ በእርግጥ እንዳመኑበት ተመለክቶ የሽባውን ሰው ኃጢአት ይቅር አለ።

- በቤቱ ውስጥ ጥቂት የሕግ መምህራን ተቀምጠው ነበር።

- ኢየሱስ የሽባውን ሰው ኃጢአት ይቅር ሲለው፣ እነዚህ የሕግ መምህራን ምን ያሰቡ ነበር?

ማርቆስ 2፡6-7

6- በዚያ ተቀምጠው የነበሩ አንዳንድ ጸሐፍት ስለዚህ ነገር በልባቸው እያሰላሰሉ፣

7- «ይህ ሰው እንዴት እንዲህ ይላል? በአምላክ ላይ የስድብ ቃል እየተናገረ እኮ ነው! ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማን ኀጢአትን ሊያስተሰርይ ይችላል?» ብለው አሰቡ።

- የሕግ መምህራን ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው ብለው ያሰቡ ነበር።

- የሕግ መምህራን በትክክል ነበር ያሰቡት?
- አዎን።

- ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ እውነት ነው?
- አዎን።

- ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችል ሰው አለ?
- የለም።

- ካህን ኃጢአትን ይቅር ማለት ይችላል?
- አይችልም።

- ኢየሱስ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ማለት የሚችለው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- የሕግ መምህራን ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየሰደበ እንደ ሆነ ያስቡ ነበር?



- የሕግ መምህራን ያሰቡት ትክክል ነበር?
- አልነበረም።

- በእውነት ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየሰደበ ነበር?
- አልነበረም።

- ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየሰደበ አልነበረም።

- ኢየሱስ፥ የሕግ መምህራኑ ምን እያሰቡ እንደ ነበር ያውቅ ነበር?

ማርቆስ 2፡8

8- ኢየሱስም ወዲያው በልባቸው የሚያስቡትን በመንፈሱ ተረድቶ፣ «እንዴት እንዲህ ታስባላችሁ አለ»? አለ።

- የሕግ መምህራን ምንም ነገር ባይናገሩም ኢየሱስ ምን ያስቡ እንደነበር ያውቅ ነበር።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ የሰዎችን ሁሉ አሳብ ያውቃል።
- ከዚያስ ኢየሱስ ምን አለ?

ማርቆስ 2፡9-12

9- ኢየሱስ እንዲህ አለ «ሽባውን፣ ‘ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል’ ከማለትና፣ ‘ተነሥተህ ዐልጋህን ተሸክመህ ሂድ’ ከማለት የቱ ይቀላል?

10- ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ለማስተሰረይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ በማለት ሽባውን፣